# የመከላከያ ሠራዊት አባላትና የአካባቢ ታጣቂዎች ተገዳደሉ

በሰሜን ጎንደር ዞን በታች አርማጭሆ ወረዳ ውስጥ ከሳንጃ ወደ ማሰሮ ደንብ በሚወስደው መንገድ በሃያ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመደበኛ የመከላከያ ሠራዊት አባላትና የማይነጋት ነውስ ወረዳ አስተዳዳሪን አጅበው በሚመጡ ታጣቂዎች መካከል በድንገት የተኩስ ልውውጥ ተካሄዶ ነሐሴ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ስድስት ተገድለው ሁለት ቆስለዋል።

በዕለቱ የኢትዮጵያ አርበኞች ግምባር ሠራዊት የመጣበት መስሎት ደንግጦ በቅድሚያ ተኩስ የከፈተው የመከላከያ ሠራዊት ሲሆን የንውስ ወረዳ አስተዳዳሪን ያጅቡ ታጣቂዎች “እኛ ጠላት አይደለንም! አትተኩሱብን እባካችሁ!” ይሉ እንደነበር ታውቋል።

የመከላከያ ሠራዊት አባላት ግን ኢያዳምጧቸው ስላልፈለጉ በተከታታይ በመተኮስ አደጋው እንዲከሰት ማድረጋቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በተኩስ ልውውጡ ከሞቱት አምሥቱ የአካባቢ ታጣቂዎች ሲሆኑ አንዱ ብቻ ከመከላከያ ሠራዊት መሆኑ ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በዚሁ በሰሜን ጎንደር ዞን በምዕራብ አርማጭሆ ውስጥ “መሬታችንን ለማንም አንሠጥም!” በማለት ለማመፅ የሞከሩ አርሶ አደሮች በአካባቢው ታጣቂዎች ተይዘው እሥራትና እንግልት እየተፈፀመባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለሱዳን በመሰጠቱ ባሁኑ ወቅት በርካታ አርሶ አደሮች ከሥራቸው ተፈናቅለዋል።